ማኑዌሊታ፣ የ ብሉ በርድ ሆቴል ባለቤት ናት፣ ወደ የአትክልት ስፍራዋ በመሄድ፣ ከልጅነት ጀምሮ እጮኛዋ የሆነውን ፔፒቶን ታስባለች። እርሱ በጦር ሰራዊት ውስጥ በ ካዲዝ እያገለገለ በመሆኑ፣ አለመኖሩን በማሰብ ታለቅሳለች። ምንም እንኳን ባለፉት አራት ወራት ውስጥ ከእርሱ ደብዳቤ ያልመጣላት ቢሆንም፣ ወይም ላለፉት ሶስት ዓመታት በአይን ባይተያዩም፣ ከሆቴሏ የምታገኘውን ትርፍ፣ ፔፒቶ ወደ ቤቱ ቶሎ ተመልሶ እንዲጋቡ ለማገዝ አስባ ስታስቀምጥ ቆይታለች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ብዙ ዓይነት የንግድ ስራዎችን የሚሰራው፣ የ ፍሉባ ተጫዋች የሆነው እና የኮሮኮዳይል ሆቴል (በከተማው ተፎካካሪ ሆቴል) ባለቤት የሆነው ቬርቲጎ ግን፣ ማኑዌሊታ ከእርሱ ጋር እንድትገናኝ እና ግዜ እንዲያሳልፉ ሊያግባባት ይሞክራል። ማኑዌሊታ ግን ለእጮኛዋ ባላት ታማኝነት በመጽናት፣ የ ቬርቲጎን መቀራረብ አልተቀበለችውም።

ቆይታ፣ ማኑዌሊታ የድሮ ጓደኛዋ የሆነውን እና ማድሪድ ከሚገኘው ኮሌጅ መጥቶ ሚስት በመፈለግ ላይ ያለው ሚጉዌል ጋር ተገናኘች። በልጅነት ያሳለፉትን ግዜ አስታወሱ፣ ሚጉዌልም እርሱ እና ማኑዌሊታ አንድ ላይ ለመሆን እጣ ፈንታቸው መሆኑን አስተዋለ። ሚጉዌልም እርሱ እና ፔፒቶ ደብዳቤ ሲጻጻፉ እንደቆዩ እና በመጨረሻው የድብዳቤ ልውውጣቸው ላይ ፔፒቶ ሊያገባ እንደሆነ እንደነገረው ነገራት። ማኑዌሊታም ይህን በሰማች ግዜ ፔፒቶ አሁንም ለኔ ታማኝ ነው ብላ በማሰብ እጅግ ደስ አላት።

ሁል ግዜም ቢሆን ችግር መፍጠር የሚወደው ቬርቲጎም፣ ሚጉዌልን ማኑዌሊታ ከእርሱ ጋር በሚስጥር ቃል ኪዳን ያሰረች በመሆኗ በመናገር ማኑዌሊታ ፈጻማ ልታፈቅረው እንደማትችል ሊያሳምነው ይሞክራል። ነገር ግን ሚጉዌል በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ሰው አይደለም። የቬርቲጎ በሆነው ዝነኛው ጋቱ ባስኩ ቁጭ ብለው፣ አንድ ብርጭቆ አፕል ሳይደር ይዘው ምግብ በሚመገቡበት ግዜ፣ ሚጉዌል ቬርቲጎ እስከሚጠግብ በልቶ በጠረጴዛው ላይ እንቅልፍ እንዲወስደው አደረገው።

አሁን ቬርቲጎ በመንገዱ ላይ የሌለ በመሆኑ፣ ሚጉዌል ለ ማኑዌሊታ ለእርሷ የሚሰማውን ስሜት በመግለጽ፣ ፔፒቶ ስለ እርሷ በጣም ግድ የሚለው ቢሆን ኖሮ እርሷን ትቶ ባልሄደ እንደነበር ገለጸላት። ይህም ማኑዌሊታ ቆም ብላ እንድታስብ አደረጋት። ይሁን እንጂ፣ ለ ፔፒቶ ባላ ታማኝነት በመጽናት፣ ሚጉዌል ስለ ፔፒቶ መጥፎ ነገር በመናገሩ ምን ያህል ስሜቷን እንደጎዳው ነገራው ብቻውን እንዲያስብ ትታው ሄደች።

ቬርቲጎ ከእንቅልፉ ሲነቃ እግሮቹ ደንዝዘው አገኛቸው። ከወንበሩ ላይ ህመም እየተሰማው ዘሎ ተነሳ፣ ሚጉዌልም ይህ ለእርሱ እንደሚገባው ምክኒያቱም ደግሞ እርሱ ከ ማኑዌሊታ ጋር ቃል ኪዳን አስረናል ብሎ ውሸት መናገሩን ነገረው። ቨርቲጎም ማኑዌሊታ "እንደማትታገሰው" አምኖ ተቀበለ። ድንገት፣ በ ፍሉባው ተጠቅሞ ሶሎ ለመጫወት ቃል ገብቶበት ለነበረው የቤተ ክርስትያን አገልግሎት እንዳረፈደ አስታወሰ! በድንጋጤ ውስጥ ሆኖ ሮጠ።

ማኑዌሊታ ከሆቴሏ ወጥታ መጣች። ሚጉዌልም ፍልጎቱ እርሷ ደስተኛ እንድትሆን ብቻ እንደሆነ በመግለጽ ይቅርታ ጠየቃት። ማኑዌሊታ ለ ፔፒቶ ባሳየቸው ታማኝነት እና ባላት የባህሪ እሴት እጅጉን በመመሰጡ፣

ፔፒቶ ወደ ቤቱ ተመልሶ ማኑዬሊታን ያገባት ዘንድ የእርሱን ቦታ ተክቶ በጦሩ ውስጥ እንዲሳተፍ በፈቃደኝነት ሄደ።

የከተማው የፖስታ ቤት ሰራተኛም ጭምር የሆነው ቬርቲጎ፣ ከ ቤተ ክርስትያን ተመልሶ በመጣ ግዜ፣ ፔፒቶ ለማኑዬሊታ ከአንድ ዓመት በፊት የላከውን ደብዳቤ እንዳገኘ ገለጸ። ሚጉዬልም ደብዳቤው በፍጥነት ተቀበሎ ባነበበው ግዜ ፔፒቶ ሌላ ሴት ማግባቱን የሚገልጽ ዜና በደስታ ተሞልቶ አነበበው።

ማኑዬሊታ በዚህ ደነገጠች። እንዴት ሆኖ ነው ፔፒቶ ሊክዳት የቻለው? ከ ብዙ መመካከር በኋላ፣ ማኑዬሊታ ለ ፔፒቶ የነበራት ታማኝነት፣ ከፍቅር የመጣ ሳይሆን፣ ከብዙ ዓመታት በፊት የገባቸው ቃል ለመጠበቅ በነበረባት ሃላፊነት የተነሳ መሆኑን አስተዋለች። ይህን ዕድሉን በመጠቀም፣ ቬርቲጎ ማኑዬሊታ እንድታገባው ጠየቃት፣ ነገር ግን ማኑዬሊታ፣ ለሚጉዌል ያላት ስሜት እውነተኛ በመሆኑ፣ እርሱን እንደምታገባ ገለጸች።

ምንም እንኳን ቬርቲጎ በዕድሉ ቢያዝንም፣ ይህን ግሩም የሆነ የንግድ ዕድል ሊያልፈው ግን አልፈለገም። በመጨረሻ አብረው መሆን በመቻላቸው ደስ ለተሰኙት፣ ለ ሚጉዬል እና ማኑዬሊታ ሰርግ የሚሆን ኬክ ለመጋገር እና ፍሉባውንም ለመጫወት ተስማማ።